## ❖ የኤርትራ መገንጠል... የባህር በር እጦት እና አንድነት

... ዘመነ መሳፍንት ተብሎ ከሚጠቀሰው የአካባቢ አፄዎች ሽኩቻ የነገሠበት የኢትዮጵያ ታሪክ ዘመን ፍፃሜ በኋላ የተቀጣጠለው የዘመናዊ ኢትዮጵያ ሀገር ግንባታ በምርጫ ሳጥን ወይም ሌላ እጣ ፈንታ መወሰኛ ዘዴ አማካይነት የህዝቦች ፈቃደኝነት እንዲኖር ተደርጎ የተካሄደ አልነበረም። ከዓለማችን መሰል ታሪኮች እንደምናየው ይህ ቢፈለግም የማይቻል ተግባር ነው። አቀጣጣይ ነዳጁም ሆነ የተገቢነት ምርኩዙ መሬት ተከል የሆነ ግዛታዊ መስፋፋት ከመሆን ውጪም አልነበረም። ማስፈፀሚያውም ብረት ጠቀስ የሆነ ኃይል፣ አስፈፃሚዎቹም በአካባቢያቸው ከሚገኙ የዘመኑ መሣፍንት ገዢዎች በተሻለ የዚህ ንብረት ባለቤት መሆን የቻሉ አፄዎች ብቻ ነበሩ። ...

------------------------------ /// ------------------------------

... የኤርትራ ከኢትዮጵያ መለየት ... ሊከሰት የማይችል የሴራ ውጤት ወይም ድንገተኛ ዱብ እዳ ነው የሚለው እጅግ ጠባብ በሆነ የታሪክ እውነታ ላይ የቆመ ትንታኔ መሆኑ በበቂ ጭብጥ የሚደገፍ ይሆናል። ... ከአፈሴላዊ እውቅና በመለስ እና መለየት ወይም ነፃ መሆን በወቅቱ ከነበረ የኢትዮጵያ አስተዳደርና ግዛት ውጪ በመሆን መልኩ ከታየ የኤርትራ መነጠል ... ከ1983ዓ.ም በኋላና በኢህአዴግ ዘመን ብቻ የሆነ ነውን? ...

------------------------------ /// ------------------------------

... በዚህ ፀሐፊ እምነት የባህር በር ለሀገራዊ ህልውና ወሳኝ ነበር። ከዛሬ አኳያ ግን ዘመን ይህን ወሳኝነቱን ነጥቆታል። በመሆኑም ከዛሬ ሀገራዊ ህይወት አንፃር መኖሩ ተፈላጊና ጠቃሚ እንጂ ህልውና ነክ ወሳኝነት የለውም። ይህንንም በግርድፉ ከታሪክ በማጣቀስ ማሳየት ይቻላል።...

------------------------------ /// ------------------------------

... የንጉሡና የዘውዱ ታማኞች ለሆኑ የአንድነቱ ኃይሎች ፌዴሬሽን መፍትሄ ሳይሆን ከጅምሩም ለዚህ ያበቃን የሚሉት "የጠላቶችና የጥቂት የውስጥ ከሃዲዎች ሴራ" ቀጣይ ፈርጅ ከመሆን የተለየ አልነበረም። በአጭሩ ፌዴሬሽን የትላንት ችግር ቀጣይነት እንጂ መፍትሄ ሆኖ አልታየም። ትርፉም ሆነ ጠቀሜታውም የተነጠለችውን ኤርትራ ከመመለስ ያላለፈ እና በዚሁ ጅምሮ ማብቃት የሚገባው ነበር። ከዚህ ውስጥ ግን ፌዴሬሽኑ በነፃነቱ ውስጥ የተካተተውን የራስ ማስተዳደር ከኢትዮጵያ ጋር ከሚኖር ህጋዊ የሆነ ሥርዓታዊ ግንኙነት ማጣመር የሚያስችል አማራጭ መሆኑን ተገንዝበው ከልብ የተቃቀፉ የተወሰኑም ነበሩ። ኤርትራን የመሰለ ብዙ የማንነት ደረጃዎች ባለበት ሁኔታ ይህ አቋም በወቅቱ የብዙኃን ባይሆንም መለስ ተብሎ ሲታይ የተሻለ ነው።

አንፃራዊ በሆነ ደረጃ ''ነፃ ኤርትራ'' የሚለውን (በጣሊያን ወይም እንግሊዝ ሞግዚትነት፣ ነፃ ሀገርነት) ጥቅል አቋም የሚያራምዱት ኃይሎች አግባቢ የሆነ ግልፅ ግብ ያልነበራቸው ከመሆኑም በላይ በድርጅታዊ ቁመና የተሰነጣጠሩ ነበሩ። የአንድነቱን ጎራ የሴራ ትንታኔ ግልባጭ በመያዝ ባላቸው አቅምና በሚገኙበት ሁኔታ ፌዴሬሽኑን በታክቲካዊ ደረጃ ተመራጭ ነው በሚል የተቀበሉ ጥቂቶች መኖራቸውንም ማየት ይቻላል። በሌላም ወገን ከአንድነቱ ጎራ ኃይል ጠቀስ መስፋፋት ወዘተ. በተያያዘ ''ከኢትዮጵያ ጋር ትስስር'' የሚል አማራጭ ተቀብለው ከተንቀሳቀሱ ብዙ ክፍያ የማይጠይቅ እና በዚህ ውስጥ ግላዊና ጎሳዊ ተጠቃሚነታቸው በተሻለ ይረጋገጣል በሚል ፌዴራሲዮኑ ሲመጣ አጋጣሚውን ለመጠቀም ወስነው የተንቀሳቀሱም ነበሩ ቢባል ተገቢ ነው። ... ትዕግስቱ ኖሮ የለዘብተኞች የፖለቲካ መስመር ከፖለቲካው መድረክ ሳይፋቅ ህያው ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ቢቻል ኋላ ላይ መተንፈሻ የሚሆን ብቻ ሳይሆን በኤርትራ ትግል ሂደት በሁሉም ላይ የበላይ እየሆነ የወጣው አንድ ኃይልና ወጥ አስተሳሰብ ሊበረዝ ወይም ቆም ብሎ እንዲያስብ የሚያስገድደው ሁኔታና አሰላለፍ እውን የመሆኑ ዕድል ጭራሹኑ ባልጠፋ ነበር። ...

----------------------------- /// -----------------------------

... በጣሊያን ቅኝ አገዛዝ መልከዓ ምድራዊ ቁመናንና ህጋዊነት ያጎናፀፉ ውሎች፤ የተለየ ፖለቲካዊ ማንነትን ለማጣቀስ እርሾ የሆኑ ተሞክሮዎችን በእንግሊዝ ሞግዚታዊ አስተዳደር፤ ቢፈለግም አማራጭ እንደማይሆን መታየቱ በቅርብ ደረጃ የሚጎተትና የፌዴሬሽኑን መፍረስ ያጀበ የተገፊነት ተሞክሮና በደል፤ የደርግ ተከታታይ ወታደራዊ ዘመቻና አፈና ያስከተለው ብሶትና እልቂት ያጎለበተው አርበኝነት የቀረፀው የኤርትራ ብሔረተኝነት ህልውናውን አገኘ። ...

----------------------------- /// -----------------------------

... የኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠል በዚህ የሀገራዊ ታሪክ ሂደት በተወሰዱ እና ባልተወሰዱ እርምጃዎች እንዲሁም ከቁጥጥር ውጪ በሆኑ ክስተቶች የተዋለደ አይቀሬ ውጤት ነው። ...